የሰበር መዝገብ ቁጥር 222120

ህዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም

ዳኞች፡-እትመት አሰፋ

ሌሊሴ ደሳለኝ

ደጀኔ አያንሳ

ሀብታሙ እርቅይሁን

እቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- ወ/ሮ ዘይነባ መሀመድ -አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ አረጋ ተወካይ መሳይ አረጋ -ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

መዝገቡ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ ለአመልካች ቤተሰቦች ለሰጠው ብድር በመያዣነት የያዘውን ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት መልቀቅ የለበትም በማለት የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09429 ነሐሴ 7 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 09815 ጥር 24 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለሆነ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ይታረምልኝ በማለት አመልካች የካቲት 25 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በማመልከታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የገጠር መሬት ይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን በተመለከተው የጊምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች በከሳሽነት ተጠሪ በተከሳሽነት የተከራከሩ ሲሆን ፤ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ይዘት መገኛው እና አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተመለከተው የአመልካች ወላጆች ይዞታ ከሆነው አንድ ሄክታር መሬት የሚች የአመልካች እናት ድርሻ የሆነውን በውርስ ለአመልካች ሊተላለፍ የሚገባውን ተጠሪ አላግባብ ይዞ የሚገኘውን የገጠር መሬት እንዲለቅላቸው ጠይዋል፡፡ ተጠሪ ይዞታው የአመልካች ወላጆች መሆኑን ሳይክድ የአመልካች ወላጆች ፤ አመልካች እና ወንድሞቿ በአንድነት ፈርመው ታህሳስ 4 ቀን 1998 ዓ/ም 3,000.00 (ሶስት ሺ) ብር ተቀብለው መሬቱ በእጁ ከገባ በኋላ የአመልካች ወላጆች ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ) ብር ተቀብለው ሰጥተውት ወደ ሌላ ሀገር ስለሄዱ የተለያዩ አትክልቶችን ተክሎ ይዞ የቆየ በመሆኑ ሊለቅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጊምቦ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ክርክር እና ምስክሮች እንዲሁም ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት አድርጎ መዝገቡን እንደመረመረው፡- መሬቱ የአመልካች እናትና አባት መሆኑ ያልተካደ ከመሆኑን በላይ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በአመልካች ወላጆች ስም መሆኑና ግብሩም በስማቸው

እንደምገበር ተረጋግጧል፡፡ ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው ውል ይዘት ለ30(ሰላሳ) ዓመት 3,000.00 በሶስት ሺ ብር ገዝቻለሁ የሚል ሲሆን ፤ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም የተደረገው ሁለተኛው ውል የአመልካች አባት መሀመድ ያሲን አይኔን ስላመመኝ ለመታከሚያ 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ) ብር ከተጠሪ ተበድሬ ብታከምም ዓይኔ ስለጠፋ *የብድሩን ገንዘብ መክፈል ስላልቻልኩኝ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ከነአትክልቱ ተጠሪ እንዲጠቀምበት ማንም እንዳይጠይቀው ሰጥተነዋል የሚል ሲሆን ፤* ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም በተደረገ ውል የአመልካች ወላጆች አከራካሪውን የመሬት ይዞታ ለ30(ሰላሳ) ዓመት በ3,000.00 (ሶስት ሺ) ብር መሸጣቸው በሰው ምስክርም ተረጋግጧል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 40(3) መሠረት መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ሆኖእያለ በተጠሪ እና አመልካቾች መካከል የተደረገው የገጠር መሬት የሽያጭ ውል ህገ መንግስቱን የሚፃረር የማይፀና ሲሆን ፤ ለ30 (ሰላሳ) ዓመት የተደረገው የኮንትራል ውሉም የኮንትራት ጊዜው ከ5(አመስት) ዓመት በላይ በመሆኑና ውሉም ሥልጣን ባለው አካል ፊት ቀርቦ ባለመመዝገቡ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 ቁጥር 8(2) (ለ) ድንጋጌን መሠረት ያላደረገ በመሆኑና ተጠሪም በአዋጁ ቁጥር 2(6) እና (7) መሠረት የአመልካች የቤተሰብ አባል ባለመሆኑ የገጠር መሬት በስጦታ ማግኘት የሚችል ስላልሆነ በተጠሪ እና የአመልካች ወላጆች መካከል የተደረገው ውል ሕገ መንግስቱ እና የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ያልተከተለ በመሆኑ ውሉ ፈርሶ ተጠሪ በውሉ የያዘውን የመሬት ይዞታ ግማሹን የአመልካች እናት ድርሻ ለአመልካች እንዲለቅ እና አመልካችም ወላጆቿ ከተቀባሉት 3,000.00 (ሶስት ሺ) ብር ግማሹን 1,500.00(አንድ ሺ አምስት መቶ) ብር ለተጠሪ እንድትከፍል ወስኗል፡፡

የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረቡትን ይግባኝ በመሰረዙ ለሁለተኛ ጊዜ የቀረበውን የይግባኝ አቤቱታ የተመለከተው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝው ሰሚው ችሎት በአመልካች ወላጆች እና በተጠሪ መካከል ለ30 (ሰላሳ) ዓመት የተደረገው የመሬት ኮንትራል ውሉ ሲሆን ፤ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) ድንጋጌ የገጠር መሬት ይዞታን በኮንትራት መስጠት በግልጽ የማይከለክል ሆኖ እያለና የኮንትራት ውሉ ሲደረግ በሥራ ላይ የነበረው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቃም አዋጅ ቁጥር 53/1995 የኮትራት ጊዜን ስላልገደበ እና አዋጅ ቁጥር 110/1999 የኮንትራት ጊዜን በአምስት ዓመት የገደበ ቢሆንም በወቅቱ ሥራ ላይ ስላልነበረ ለጉዳዩ አግባቢነት የሌለው በመሆኑ ውሉ ሕገ - ወጥ ነው የሚባልበት አግባብ የለም፡፡ ውሉ ሕገ - ወጥ ነው ቢባል እንኳን በሁለት ዓመት ውስጥ መቃወሚያ ስላልቀረበ የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ሲገባ የወረዳ ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ ተገቢነት የሌለውን ሕግ ጠቅሶ የሰጠውን ውሳኔ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱም አለማረሙ መሠረራዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔን ሽሮ ፤ ተጠሪ ለ30(ሰላሳ) ዓመት በኮንትራት የያዘውን መሬት የኮንትራት ጊዜው ሳይደርስ ሊለቅ አይገባም በማለት በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡ አመልካች ውሳኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመት ነው በማለት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የሥር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰጣ ችሎትም የአመልካችን አቤቱታ ባለመቀበል የይግባኝ ሰሚ ችሎቱን ውሳኔ ስላፀና አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው የመጀመሪያው ውል ለ30(ሰላሳ) ዓመት በ3,000.00 (በሶስት ሺ) ብር ሽጠንለታል የሚል ግልጽ የመሬት ሽያጭ ውል ሲሆን ፤ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም የተደረገው ሁለተኛው ውልም ለዓይን ህክምና የወሰዱት 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ) ብር ብድር መክፈል ስላልቻልን ሰጥተናል

የሚል በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ግንኙነት ለተፈጠረ ዕዳ አርሶ የሚጠቀሙበትን ባዶ የገጠር መሬት ለዕዳ መያዣነት የማይውል በመሆኑና የቤተሰብ አባል ላልሆነ ሰው መሬት በስጦታ የማይሰጥ መሆኑን የሰበር ሰሚ ችሎቱ በተለያዩ መዛግብት ላይ የሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔዎችንና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሰጠውን የሕገ መንግስት ትርጉም በሚፃረር መልኩ ተጠሪ መሬቱን የያዘው በሕገ ወጥ ውል አይደለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀበት ነው፡፡ ውሉ የኮንትራት ውል አይደለም እንጂ ነው ቢባል እንኳን ሥልጣን ባለው አካል ፊት ስላልተመዘገበ እና 30 (ሰላሳ) ዓመት የኮትራት ጊዜውም እጅግ የበዛ አርሶ አደሩን ከይዞታው ላይ የሚያፈናቅል ሆኖእያለ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሕገ መንግስታዊ የመሬት ባለይዞታነት መብትን የሚፃረር በመሆኑ የሰበር ሰሚውና የይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሸሮ የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝና የጊምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

አመልካችን ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ የመረመረው የሰበር አጣሪ ችሎቱ የኮንትራት ውሉ ሕጋዊ ነው ተብሎ የመወሰኑ አግባብነት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስቱ አንቀጽ 40 ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 49200 እና ተያያዥ ትርጉሞች ፤ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በአለሚቱ ገብሬና ጫኔ ደሳለኝ ክርክር ከሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ፤ እንዲሁም የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ አንፃር ለማጣራት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ ምላሽ እንዲሰጡ ታዘው በሰጡት መልስ፡- በግራ ቀኙ መካከል ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም ለ30(ሰላሳ) ዓመት የተደረገው የኮትራት ውሉ በጊዜው በሥራ ላይ የነበረው አዋጅ ቁጥር 53/1995 የኮትራት ጊዜን ስለማይገደብ እና ሕገ መንግስቱትም ኮንትራን ስለማይከለክል ውል በሕግ ፊት የፀና በመሆኑ አመልካች የኮንትራት ጊዜው ሳይጠናቀቅ መሬቱ እንዲለቀቅላቸው ክስ የማቅረብ ሕጋዊ መብት የላቸውም፡፡ ተጠሪ መሬቱን የያዝኩት በዕዳ ማቻቻያነት ሳይሆን በኮንትራት በመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 49200 ሆነ የፌዴሬሽ ምክር ቤት በወ/ሮ አለሚቱ ገብሬና አቶ ጫኔ ደሳለኝን አስመልክቶ የሰጠው የሕገ መንግስት ትርጉም ከተያዘው ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት በሌለው ጉዳዩ ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ባለመሆኑ ለሰበር አቤቱታው ምክንት የሆነው ውሳኔ ምንም የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በመልስ መልሳቸው የውሎቹ ይዘት በተጠሪ ያልተካዱ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፋ ሲል የተመለከተው ሲሆን ችሎቱም በግራቀኙ መካከል ያለው ውል የትኛው እንደሆነ ? ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው ነው ወይስ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም የተደረገው ፤ እንዲሁም ተጠሪ የመሬቱ ባለይዞታ ሆንኩበት የሚለው ውል በቦታው ላይ ባለይዞታ ሊያደርገው የሚችል መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ ፤ አስገዳጅ የሰበር ውሳኔ አንፃር የውሎቹ ይዘት እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አስቀድሞ የነበረው የውል ግዴታ በአዲስ ለመተካት ተዋዋዮች ከስምምነት የደረሱ እንደሆነ ነባሩ ግዴታ ቀሪ እንደሚሆን ከፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1807 (ሐ) እና 1826 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ወላጆች እና በተጠሪ መካከል ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም እና ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም በአከራካሪው የመሬት ይዞታ ላይ ሁለት የተለያየ ይዘት ያላቸው ውሎች የተደረጉ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የጊምቦ ወረዳ ፍርድ ቤት

በአመልካች ወላጆች እና በተጠሪ መካከል ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው ውል የመሬት ሽያጭ ውል በመሆኑና የ30 (ሰላሳ) ዓመት የኮንትራት ጊዜም በሕጉ ከተቀመጠው ገደብ በላይ ስለሆነ እና ውሉም ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ ስላልተመዘገበ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት እና የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጁ የሚፃረር በመሆኑ ሊፀና አይገባም በማለት ተጠሪ አከራካሪውን ይዞታ እንዲለቅ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገውን ውል በመመርመር ውሉ ለ30 (ሰላሳ) ዓመት የተደረገ የመሬት ኮንትራት ውሉ ሆኖ ህገ መንግስቱ የገጠር መሬት ይዞታን በኮንትራት መስጠትን ስለማይከለክል እና በወቅቱ በሥራ ላይ የነበረው የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅም የኮንትራት ጊዜን ስላልገደበ ውሉ ሕገ ወጥ ነው የሚባልበት የሕግ አግባብ የለም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ሽሯል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤቶች የመረመሩት ውል በአመልካች ወላጆች እና በተጠሪ መካከል ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገውንና ተዋዋዮቹ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም ባደረጉት ውል ተተክቶ ቀሪ የሆነውን ግዴታ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ቀሪ የሆነውንና በተዋዋዮቹ ላይ የአስገዳጅነት ኃይል የሌለውን ውል ሕጋዊነት መርምሮ ውሳኔ መስጠታቸው የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

አስቀድሞ ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገው ውል ቀሪ ሆኖ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም በተደረገ አዲስ ውል ስለተተካ ፤ የዚህ ውል ይዘትና በሕግ ፊት የፀና መሆን አለመሆኑን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም የተደረገው ውል ይዘት የአመልካች አባት የሆኑት አቶ መሀመድ ያሲን “አይኔን ስላመመኝ ለመታከሚያ 100,000.00 (አንድ መቶ ሺ) ብር ከተጠሪ ተበድሬ ብታከምም ዓይኔ ስለጠፋ የብድሩን ገንዘብ መክፈል ስላልቻልኩኝ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ከነአትክልቱ ተጠሪ እንዲጠቀምበት ማንም እንዳይጠይቀው ሰጥተነዋል “ የሚል እንደሆነ የጊቦ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ የገጠር መሬትን ለዕዳ መክፈያነት በመያዝ በውል ማስተላለፍ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዩጵያ ብሔር ፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሀብት ነው ከሚለው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40(3) ጋር የሚጣረስ እና በፍትሐ ብሔር ሕጉ ቁጥር 1678 (ለ) መሠረትም ውሉ ሕጋዊ በሆነ ጉዳይ ላይ የተደረገ ባለመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የሌለው እና መብትን እንደማያጎናጽፍ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 49200 ላይ ህዳር 1 ቀን 2002 ዓ/ም የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 ቁጥር 10(2) መሠረት በየትኛውም ደረጃ የሚገኘውን የፌደራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤት የሚያስገድድ ሆኖእያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ይህን በመተላለፍ የሰጡት ውሳኔ ሊታረም የሚገባ ነው፡፡

ሲጠቃለል የአመልካች ወላጆች እና ተጠሪ አስቀድሞ ያደረጉት ውል በሌላ አዲስ የውል ግዴታ ተክተው እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ እልባት ከመስጠት አንፃር ተገቢ ያልሆነውን ታህሳስ 1 ቀን 1998 ዓ/ም የተደረገውን ውል መርምሮ ውሳኔ መስጠታቸው ሆነ ተጠሪ በይዞታው ላይ ባለመብት አድርጎኛል የሚለው ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም የተደረገው ውል የባለይዞታነት መብት የሚያጎናጽፈው መሆን አለመሆኑን ሳይመረምሩ አልፈው የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ቀጣዩ ተወስኗል፡፡

ውሳኔ

1. የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቅጥር 09815 ጥር 24 ቀን 2014 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 (1) መሰረት **ተሽሯል**፡፡
2. የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጋቢት 30 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 19595 የሰጠው ትዕዛዝ እና የጊቦ ወረዳ ፍርድ ቤት መጋቢት 21 ቀን 2013 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር19583 የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ በውጤት አንባር ፀንቷል፡፡
3. በአመልካች ወላጆች እና ተጠሪ መካከል ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ/ም የተደረገው የገጠር መሬትን የብድር ዕዳን ለማስመለስ የተደረገው የመያዣ ስምምነት በሕግ ፊት የሚፀና ውል አይደለም በማለት ተወስኗል፡፡
4. ተጠሪ በሕግ ፊት በማይፀና ውል መነሻነት የያዘውን ይዞታ መሬት የአመልካች እናት ድርሻን ለአመልካች እንዲለቅ ተወስኗል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
6. ግራ ቀኞቸው የሰበር ክርክሩ ያስከተለው ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ተብሏል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ን

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

https://lawethiopiacomment.wordpress.com/